# <u>እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1-10/2019 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፉት በጃንዋሪ አስር ቀናት የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ ነበር የቀጠለዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ይበልጥ ከመጨመሩም ባሻገር የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀትም በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በጥቂት ቦታዎች ላይም ከዜሮ ዲ.ሴ. በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በባቲ -3.0፣ በደብረብርሃን -1.5፣ በጅማ -1.2፣ በሀረማያ 0.8፣ በወገልጤና 1.4፣ በመቀሌ 2.5፣ በባሌሮቤ 3.5፣ በቡኢ 3.6 እና በአምባማሪያም 3.6 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ አልፎ አልፎ ሳሳ ያለ የደመና ሽፋን ተስተዉሎባቸዋል፡፡

በአሥሩ ቀናት ውስጥ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በደረቅ የአየር ሁኔታ ስር እንደቆዩ ከአየር ሁኔታ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1 እና 2 )።

በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3)።

ካርታ1   እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



**ካርታ3   እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**



ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# <u>እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1- 10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

ባለፉት የጃንዋሪ የመጀመሪያው አስር ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ በአንዳንድ ድህረ ሰብል ስብሰባ ባልተጠናቀቀባቸው የመኸር አብቃይ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑት የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አይሎ ነበር የተስተዋለዉ፤ ከቅዝቃዜው መጨመር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሸየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም እንደ ባቲ ፣ ደብረብርሃን እና ጅማ አካባቢዎች ከዜሮ ዲ.ሴ. በታች (ከ -1.2 እስከ -3.0) በዲ.ሴ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ በቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4) ፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1-10/2019 የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1-10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 01-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በአብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማና ፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደራቃማ የአየር ሁኔታ አመዘኖ ቆይቶ ነበር (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2019 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2019 የሚኖረው

## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ አመዝኖ ይቆያል። ይሁን እንጂ አንዳንድ የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ ሥፍራዎች ለጥቂት ቀናት አነስተኛ ዝናብ ያገኛሉ።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደራቃማ የአየር ሁኔታ እያመዘነ እንደሚቆይና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም በደጋማ አካባቢዎች ላይ ጥንካሬው ጎልቶ እንደሚታይ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ ሁለተኛው የጃንዋሪ አስር ቀናት በአመዛኙ ከሚስተዋለው ደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው መኸር አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚከናወኑበት ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ በሂደት ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡

ከላይ በተሰጠው የአስር ቀናት የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የጃንዋሪ ሁለተኛዉ አስር ቀናት በብዙ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት እንደሚኖረው በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመልክቷል፡፡ በተለይም የሚጠበቀው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩም ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ቅዝቃዜው በቀጣይነት እንደሚስታዋል የትንበያ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በተወሰነ መልኩ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎች፤ በጓሮ አትክልቶችና በእንስሳት ምርት ላይ አሉታዊ ጎን እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም

አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸዉ አካላት እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራት በማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## <u>እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ፀሃያማ፣ ነፋሻማና ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የትንበያው መረጃዎች ይጠቁማል፡፡ በዚህ መሰረት በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ የማለዳው ቅዝቃዜ መኖር የአማካኝ የቀኑ ሙቀት አነስተኛ እንዲሆን አስተዋፅዖ በማድረጉ ለውሃ አካላት ትነትን በመቀነስ በኩል በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡